# የኢትዮጵያዊያን
# አንድነት ዕድር መተዳደሪያ ደንብ



**Mailing Address**
**7052 Santa Teresa Blvd #105**
**San Jose, Ca 95139**

ድር ቢያብር አንበሳ ያስር” የአባቶቻችን መሪ ቃል ነው። በዚህ የተነሳ በዕድሩ፣ በማኅበሩ፣ በዕቁቡ ተሳስረው በጋራ ማኅበራዊ ኑሮአቸውን ይመሩ ነበር። እኛም በሰሜን አሜሪካ፣ በካሊፎርኒያ ግዛት፣ በሳንሆዜ አካባቢ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮ-አሜሪካዊያን ለብዙ ጊዜ የምንመኘውን ይህን ዕድር አቋቁመናል። ዕድራችንን ማዳበር፣ኅብረታችንን ማጠናከር የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

**የካቲት 29 ቀን 2007 ዓ.ም (March 01/2015)**

# የኢትዮጵያውያን አንድነት ዕድር መተዳደሪያ ደንብ

## መ ግ ቢ ያ

እኛ በሰሜን አሜሪካ በካሊፎርንያ ግዛት በሳን ሆዜና አካባቢው ከተሞች የምንገኝ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮ -አሜሪካውያን ለብዙ ጊዜ ስንመኘው የነበረውን የመረዳጃ ዕድር አቋቁመናል። ዕድር ለተለያዩ አገልግሎቶች በተለያየ መልክ እየተመሰረተ ሲያገለግል የኖረ ባህላዊ እሴታችን ነው። ይህም እንደየተግባሩ በመተዳደሪያ ደንብ ይገለጻል።

አሁንም የእኛ ዕድር አላማውና ተግባሩ ከታች እንደሚያስረዳው አንድ መብትና ግዴታውን ያሟላ አባል በራሱም ሆነ በቤተሰቡ ላይ የሞት አደጋ በሚደርስበት ጊዜ ዕድሩ ፈጥኖ በመድረስ ደንቡ በሚፈቅደው መሠረት የገንዘብ ፣ የሃሳብና የጉልበት እርዳታ ለቀሪው ቤተሰብ በማድረግ አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ እንዲያደርግለት የተቋቋመ ዕድር ነው።

ይህ ከአንቀጽ 01 እስከ አንቀጽ 17 የተካተተ ደንብ ለኢትዮጵያ አንድነት ዕድር መተዳደርያ ደንብ ሆኖ ያገለግላል።

# ክፍል አንድ

## ትርጉም

1. ዕድር ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሞት አደጋ በሚደርስበት ወቅት በገንዘብና በሞራል ለመረዳዳት የተቋቋመ ማሕበራዊ አገልግሎት መስጫ ነው።

2. ዕድርተኛ ማለት የዕድሩን ሕግና ደንብ ተቀብሎ አባል የሆነ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ነው።

3. ቤተሰብ ማለት ባል ሚስት እና እስከ 21 ዓመት ድረስ ያሉ ልጆችን ያካትታል።

4. ባልና ሚስት ማለት በሕግ ተጋብተው ሳይፋቱ በአንድ አድራሻ የሚኖሩና በዕድሩ ማመልከቻ ላይ ስማቸው የተጠቀሰው አባል ነው።

5. ልጆች ማለት እድሜያቸው ከትውልድ እስከ 21 አመት የሆኑ ከወላጆቻቸው ጋር አብረው በአንድ አድራሻ የሚኖሩ ወይንም በተለያየ የአሜሪ ካግዛት ያሉትን ያካትታል።

   5.1 በተጨማሪ እድሜያቸው ከ21 አመት በላይ የሆኑ የእድሩ አባል ልጆች በግል አባል መሆን ከፈለጉ በቤተሰብ የሚያገኙት የእድሩ ጥቅም በተቋረጠ

በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ያለምንም የመመዝገቢያ ክፍያ የወረሃዊ ክፊያ ብቻ በመክፈል በግላቸው የእድሩ አባል መሆን ይችላሉ።

6. እንግዳ ማለት በማንኛውም ጊዜ ከሌላ አካባቢ ለጉብኝት ወይም ለጥየቃ በእድርተኛው መኖሪያ ቤት እስከ ስድስት ወር የሚቆይ ጊዜያዊ ነዋሪ ማለት ነው ከስድስት ወር በላይ በእድርተኛው አድራሻ የሚቆይ ከሆነ ግን እንግዳ አይባልም። ይህም ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ እድሩ ማስረጃ ሊጠይቅ ይችላል።

7. በወንድ ጾታ የተገለጸ ሁሉ ለሴትም ያገለግላል።

# ክ ፍ ል ሁለት የዕድሩ መግ ለጫዎች

## አንቀጽ 1 - ስያሜ

ዕድሩ የኢትዮጵያውያን አንድነት ዕድር ተብሎ ይጠራል።

## አንቀጽ 2 - የዕድሩ አድራሻ፤

የዕድሩ አድራሻ በካልፎርንያ ግዛት በሳንታ ክላራ ካውንቲ ሳን ሆዜ ከተማ ነው።

## አንቀጽ 3 - የዕድሩ ዓላማ

3.1 በሳን ሆዜና አካባቢዋ የምንኖር ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮ -አሜሪካን አገር በቀልና ፍቱን በሆነው ባህላችን በዕድር ተደራጅተን በሞት አደጋና በቀብር ጊዜ በሀሳብ በገንዘብና በጉልበት ለመረዳዳት፤

3.2 ዕድርተኛው ወይም ባለቤቱ እንዲሁም ልጆቹ በጸና ታመው ራሳቸውን ለመርዳት ከአቅም በላይ የሆነ ደረጃ ሲደርሱ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ለመጠየቅና አስፈላጊውን ትብብር ለማድረግ፤

3.3 ዕድርተኛው የሟቹ አስክሬን ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄድ ከወሰነ ደንቡ በሚፈቅደው መሰረት አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ፤

3.4 የሚረዳዳና የሚተሳሰብ ሕብረተ -ስብ ለመገንባት የሚያስችሉ ተግባራትን ሁሉ ለማከናወን፤አግባብ ካለቸው አካለት ጋር ተገቢውን ለመፈጸም፤

3.5 አገር በቀል የሆነውንና ለረጅም ዘመን የተፈተነውን ባህላችንን ለልጆቻችን ለማስተላለፍ፣ ጠንካራና ጤናማ ቤተሰብ ለመመስረት ነው።

## አንቀጽ 4 - የዕድሩ የሕግ ሰውነት

4.1 በካሊፎርንያ ግዛት ሕግና ደንብ መሠረት ፈቃድ ከአገኘበት ጊዜ ጀምሮ የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ይኖረዋል።

4.2 ይህ ዕድር በአባላቱ መዋጮና ከልዩ ልዩ እርዳታ ሰጪዎች በሚገኘው ገቢ ይተዳደራል። አትራፍፊ ያልሆነ (None Profit) ድርጅት ሆኖ ይቀጥላል።

4.3 ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውንም ውል ይዋዋላል፣ይከሳል፣ይካሰሳል፣ያስተዳድራል::

4.4 ይህ ደንብ የመንግስትን ሕግጋት በማይጻረር ሁኔታ ወይም የመንግስትን ሕግና ደንብ የሚያዘውን ተከትሎ የተዘጋጀ ነው።

# ክ ፍ ል ሦስት

## አንቀጽ 5 - አባል ስለመሆን

5.1 ዕድሩ የዘር፣የሃይማኖት፣ የቀለም ፣ የጾታና የፖለቲካ ልዩነት አያደርግም።

5.2 እድሜው 18 ዓመትና ከዚያም በላይ የሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ የዕድሩ አባል ለመሆን ጥያቄውን በጽሑፍ ወይም በተዘጋጀው መጠየቂያ ያቀርባል።

5.3 የዕድሩን መተዳደሪያ ደንብ አምኖ የተቀበለና ሌላም አስፈላጊ ጥያቄዎችን ቦርዱ አቅርቦለት አስተማማኝ ሆኖ ካገኘው በአባልነት ይመዘግበዋል ፣ የአባልነት መታወቂያም ይሰጠዋል።

5.4 አንድ ዕድርተኛ ሙሉ የአባልነት መብቱ የሚጠበቅለት፣ ለአስራ ሁለት ወር (ለአንድ ዓመት) ክፍያዎችን አጠናቆ በተከታታይ ሲከፍል ነው።

5.5 የአባልነት ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘ አባል በእየጊዜው ራሱንና ቤተሰቡን የሚመለከቱ ለውጦች ሲኖሩ ለዕድሩ የተዘጋጀውን የመመዝገቢያ ቅጽ እየሞላ ማሳወቅ አለበት።

5.6 ዕድሩ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ካከበተ በኋላ አባልነት የተፈቀደለት ሁሉ፣በአስተዳደር ቦርዱ ታስቦ የሚጠየቀውን መክፈል አለበት።

# አንቀጽ 6 - የምዝገባ ሥነ-ሥርዓት

ማንኛውም አመልካች የዕድሩ አባል ሆኖ ለመመዝገብ ከዚህ በታች የተዘረዘረውን በመጀመሪያ አሟልቶ መገኘት አለበት።

6.1 የዕድር አባልነት መጠየቅያ ቅጾችን ሞልቶ ማስገባት።

6.2 ማንኛውም አዲስ አባል በዕድርተኛነት ሲመዘገብ የዕድሩ ተጠቃሚ የሚሆኑትን የቤተሰብ አባላት ጨምሮ በተዘጋጀው ቅጽ ሞልቶ ማስመዝገብና እንደአስፈላጊነቱ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

# አንቀጽ 7 መብት

7.1 አንድ ዕድርተኛ የመመረጥ የመምረጥና ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ መብት አለው።

7.2 አንድ አባል 12 ወር በአባልነት ከቆየ በኋላ በደንቡ መሠረት ባስመዘገባቸው ቤተሰቦች ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ ደንቡ የሚፈቅደውን ማንኛውንም ጥቅም የማግኘት መብት አለው።

7.3 አንድ የዕድር አባል ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ እንደ አባላቱ ፍላጎት የቀብር ሥነ ስርዓቱን ለማስፈጸምም ሆነ አስከሬኑን ወደ ሐገር ቤት የሚላክበትን ወጪ ለመሸፈን ይረዳ ዘንድ ከኤፕሪል 1 ቀን 2023 ዓ/ም ጀምሮ በሰው $20,000 (ሃያ ሺህ ዶላር) ከዕድሩ ሂሳብ ወጪ ሆኖ እንደሚከተለው የሚከፈል ሲሆን ወደፊት የክፍያው መጠን እንደ አስፈላጊነቱ በጠቅላላ ጉባዔው ሊለወጥ ይችላል።

## የገንዘቡ አከፋፈል

ሀ. ባል ከሞተ ለሚስት

ለ. ሚስት ከሞተች ለባል ሲሆን

ሐ. ወራሽ ከሌለ ግን አባሉ በማመልከቻው ላይ በጠቀሰው ኑዛዜ መሠረት በአንቀጽ 8.8 እንደተደነገገው የዕድሩ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ (ቦርድ) የቀብር ሥነ ሥርዓቱን ያስፈጽማል።

7.4 በአንድ የእድር አባል ላይ በመኖሪያ ቤቱ የእድሩ ዋና ጥቅም ተከፋይ ባልሆኑ ወይም (none eligible) በሆኑ የቤተሰብ አባላት ወይም እንግዳ ላይ የሞት አደጋ ሲያጋጥም አደጋው ባጋጠመበት የእድሩ አባል ቤት ለአስከሬን መሸኛ ይረዳ ዘንድ ለእድሩ አባል $2,000.00 ዶላር ይሰጠዋል።

7.5 አንድ ዕድርተኛ የአባልነት የወር ክፍያውን ለመክፈል ለጊዜው በሕመም ሆነ በተለያዩ የግል ችግሮች ምክንያት አቅም አጥቻለሁ ብሎ ለቦርዱ በጽሑፍ ካስታወቀና ቦርዱም የአባሉን ጥያቄ አጥንቶና ተወያይቶበት ለጊዜው መክፈል አለመቻሉን ከተረዳ ጉዳዩ ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ሲወሰን ሥራ እስከሚያገኝ ድረስ ወይም ለአንድ ዓመት ያህል በነጻ አባል ሆኖ ይቆያል ክፍያውንም በደንቡ መሠረት ይከፈለዋል።

7.6 በድንገተኛ አደጋ ወይም በሽታ በሐኪም የተመሰከረ ቋሚ ሕመም ወይም በሽታ ካጋጠመውና በገቢ እጥረት ምክንያት የወር ክፍያውን መክፈል ካልቻለ ቦርዱ ያለክፍያ አባል ሆኖ እንዲቀጥል ያደርገዋል።

7.7 አስከሬኑን ለመቅበር ወይም ወደ ሌላ ቦታ ለመሸኘት በሚደረገው ሥርዓት ላይ ዕድርተኞች በሙሉ በሃዘንተኛው ቤት በመገኘት ያጽናናሉ ወይም ይተባበራሉ።

7.8 የሚቹ ቤተሰቦች ለእዝን በተቀመጡበት ቤት በመገኘት ዕድርተኞች ሀዘንትኞቹን ያስተዛዝናሉ ያስተናግዳሉ።

7.9 ከላይ በአንቀጽ 7.7 እና 7.8 የተጠቀሰው ሥነ-ሥርዓት በሚከናወንበት ጊዜ ከሃዘንተኛው ቤተሰብም ሆነ ከቦርዱ የሚሰጣቸውን የሥራ ድርሻ /ፕሮግራም በኃላፊነት ይወጣሉ።

7.10 ከፍተኛ አደጋ የደረሰበትን፤በጠና የታመመ አባልን በመጎብኘት ቤተሰቡ የሚረጋጋበትን፣የሚረዳበትን መንገድ መተለም አለባቸው።

7.11 አንድ አባል ባለቤት ከሌለው ከልጆቹ መካከል ለአንደኛው ልጁ ብቻ ለማን ማውረስ እንዳለበት በማመልከቻው ላይ ማስመዝገብ አለበት

7.12 በዚህም መሠረት ከአንድ አባል በላይ መቀበል አይቻልም።አራት ልጆች ቢኖሩት አንዱ ከወረሰና ከሞተ ሌላ መቀበል አይችልም ለማለት ነው።

7.13 አንድ የቅርብ ቤተሰብ ማለት በወንድሞችና እህቶች የዕድር አባላት መካከል የጋራ ዘመድ የሞት አደጋ በሚደርስበት ጊዜ በሕገ ደንቡ ላይ የተጠቀሰው እርዳታ የሚሰጠው በአንቀጽ 7.4 በተደነገገው መሠረት ነው።

7.14 ባልና ሚስት ከተፋቱ ሁለቱም አዲስ የማመልከቻ ቅጽ በየስማቸው ሞልተው በአባልነታቸው መቀጠል ይችላሉ በዚህም ወቅት ተጨማሪ የመመዝገቢያ ክፍያ አይጠየቁም።

7.15 አንድ አባል በሥራ ወይም በሌላ ጉዳይ ወደ ሌላ ግዛት ቢዛወር በወኪል አማካኝነት አባልነቱን ሊቀጥል ይችላል።

7.16 አንድ አባል በዕድርተኛነት መቀጠል ካልፈለገ የማቆም መብቱ የተጠበቀ ሲሆን ለአባልነት የከፈለውን ገንዘብ ይመለስልኝ ብሎ መጠየቅ አይችልም።

7.17 አንድ አባል በማንኛውም ምክንያት ወደሌላ ከተማ፤ግዛት ሂዶ ቢሞት ለመሞቱ ሕጋዊ ማስረጃ እስከአቀረበ ድረስና የሚፈለግበትን ክፍያ በደንቡ መሠረት አሟልቶ ከተገኘ ክፍያው ይሰጠዋል።

7.18 አንድ አባል አካበቢውን ለቆ ወደ ሌላ ከተማ ፤ግዛት ከሂደና በደንቡ መሠረት ክፍያውን ከቀጠለ የአባልነት መብቱ ይጠበቅለታል ሆኖም ግን በአንቀጽ 7.7 እና 7.8 የተጠቀሰውን ለማድረግ አይገደድም አባላቱም ለእርሱ አይገደዱም።

7.19 ዕድሩ የመጀመሪያ ዓመቱን ካከበረ በኋላ የሚገባ አባል $300 (ሦስት መቶ ዶላር) የመመዝገቢያ ክፍሎ የጥቅሙ ተከፋይ ለመሆን እንደማንኛውም የዕድር አባል አንድ ዓመት መጠበቅ አለበት።

# አንቀጽ 8 - ግዴታ

8.1 የዕድሩ ደንብ የሚጠይቀውን ግዴታዎች መፈጸም።

8.2 አስገዳጅ ሁኔታ ካላገጠመ በስተቀር በጠቅላላ ስብሰባ ላይ መገኘት።

8.3 ለመጀመሪያ ጊዜ መመዝገቢያ ዕድርተኛው $300.00 (ሦስት መቶ ዶላር) ይከፍላል።

8.4 የአባልነትን የወር መዋጮ ከጃንዋሪ 2024 ጀምሮ $30.00 (ሰላሳ ዶላር) በወቅቱ መክፈል።

8.5 በዕድርተኞች መካከል መቀራረብ፣መፈቃቀር፣መተሳሰብና መረዳዳት እንዲሰፍን እያንዳንዱ አባል አስተዋጽኦ የማድረግ ግዴታ አለበት።

8.6 እያንዳንዱ አባል መዋጮውን በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ አጠናቆ የመክፈል ግዴታ አለበት፡

8.7 አንድ አባል ሲሞት ዕድርተኞች የሚቹን ቤተሰብ የማስተዛዘን፤የማስተባበር፤ የመቅበር ወይም የመሸኘት ግዴታ አለባቸው፡ :

8.8 አንድ ቤተሰብ ወይም ወኪል የሌለው አባል በሚያርፍበት ጊዜ የዕድሩ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ደንቡ በሚያዘው መሠረት የቀብሩን ሥነ -ሥርዓት ይፈጽማል።

8.9 የአባላት ወራሃዊ ክፍያ ከጃንዋሪ 2024 ጀምሮ $30.00 (ሰላሳ ዶላር) ሲሆን ክፍያው በአመት ሁለት ጊዜ ብቻ ማለትም ከጃንዋሪ 1 እስከ ጃንዋሪ 31 ድረስ ያለ ቅጣት $180.00 ዶላር እንዲሁም ከጁላይ 1 እስከ ጁላይ 31 ድረስ ያለቅጣት $180.00 ዶላር እንዲከፈል ወይም የአመቱን በአንድ ጊዜ ክፍያ $360.00 ዶላር እንዲከፈል ሲሆን ነገር ግን ከተቀመጠው ቀነ ገደብ ያሳለፈ አባል ማለትም ከፌብሩዌሪ 1 ወይም ከኦገስት 1 በኋላ በተጨማሪ $50.00 ዶላር ቅጣት ጋር ይከፍላል።

8.10 ክፍያውን በተወሰነው ጊዜ የማይከፍል አባል $50 መቀጫ ይከፍላል ነገር ግን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ለምሳሌ ያህል በሆስፒታል ተኝቶ፣እስር ቤት ገብቶ፣ በአዕምሮ በሽታ ታውኮ ከሆነ መቀጫውን እንዳይከፍል ይቅርታ ይደረግለታል ይህም ሊሆን የሚችለው በቂ ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ ነው።

8.11 በአንቀጽ 8.10 የተጠቀሰው ችግር ሳያጋጥመው የስድት ወር ክፍያውን ሳያሟላ አንድ አደጋ በዕድርተኛው ወይም ቤተሰቡ ላይ ቢደርስ በሕጉ መሠረት የተመደበውን ክፍያና እርዳታ ማግኘት አይችልም።

8.12 ደንቡ በሚፈቅደው መሰረት የመመዝገቢያውንና የወር ክፍያውን በወቅቱ መክፈል አለበት።

8.13 ዕድሩ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ካከበተ በኋላ አባልነት የተፈቀደለት ሁሉ፣ በአስተዳደር ቦርዱ ታስቦ የሚጠየቀውን መክፈል አለበት።

8.14 በጉልበትም ሆነ በሃሳብ በሚመደብበት ሁሉ ዕድሩን ለማገልገል ፈቃደኛ መሆን አለበት።

## አንቀጽ 9 - ከአባልነት ማቋረጥ

9.1 ከዕድር አባልነቱ መልቀቁን በጽሁፍ ለአስተዳደር ቦርዱ አሳውቆ የተሰጠውን የዕድር አባልነት መታወቂያውን ሲመልስ።

9.2 ብቸኛ የነበረ ከሆነ ራሱ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ፣ወይም ሁለቱም ባልና ሚስት ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩና ሕጋዊ ወራሽ ሳይኖራቸው ሲቀር።

9.3 በዚህ ደንብ መሠረት የሥነ -ሥርዓት እርምጃ ሲወሰድበት።

9.4 ወደ ሌላ ግዛት ለቆ ከሄደና ወርሀዊ ክፍያውን ካቋረጠ እንዲሁም በአንቀጽ 9.1 እና 9.3 የተጠቀሰው ከተፈጸመ ቀደም ብሎ የከፈለው ገንዘብ ይመለስልኝ ብሎ መጠየቅ አይችልም።

# አንቀጽ 10 - ወደ አባልነት ስለመመለስ

10.1 አንድ አባል እስከ ስድስት ወር ድረስ ያልከፈለ ከሆነ ክፍያውን ከአቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ከሃምሳ ብር መቀጫ ጋር በአስራ አምስት (15) ተከታታይ ቀናት ውስጥ ከከፈለ አባልነቱን መቀጠል ይችላል።

10.2 አንድ አባል ከ ስድስት ወር በላይ ያልከፈለ ከሆነ ከዕድሩ በገዛ ፈቃዱ እንደለቀቀ ይቆጠራል ሆኖም ግለሰቡ በአዲስ መልክ ወደ ዕድሩ ተመልሶ መግባት ከፈለገ የአስተዳደር ቦርዱ ማመልከቻውን በመመልከት ወደ አባልነቱ እንዲመለስ ሊፈቅድለት ይችላል ይህም ሲሆን ተጠቃሚ ለመሆን በአንቀጽ 5.4 በተደነገገው መሠረት አንድ ዓመት መጠበቅ ይኖርበታል።

10.3 የዕድሩን ሕግና ደንብ ተላልፎ የሥነ -ሥርዓት እርምጃ ተወስዶበት የተወገደ ከሆነ ግን ወደ ዕድሩ የመመለስ እድል የለውም።

# አንቀጽ 11 - የሥነ ሥርዓት እርምጃ

ግዴታውን ባልተወጣ አባል ላይ እንደየጥፋቱ መጠን የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

11.1 የስድስት ወር ክፍያ በተከታታይ ያልከፈለ የአባልነት መብቱ አይጠበቅለትም።

11.2 የከፈለው ገንዘብ ወይም ያበረከተው ንብረት አይመለስለትም።

11.3 አንድ አባል በዕድሩ ስብሰባ ላይ ወይም የአስተዳደር ቦርዱ የሚያካሂደውን የዕድር ሥራ ለማደናቀፍ ሲሞክር ወይም በስውር ዕድሩን የሚጎዳ ሁኔታ ሲፈጽም በማስረጃ ከተረጋገጠ ቦርዱ ጉዳዩን መርምሮና ጥፋተኛ ሆኖ ሲያገኘው እንደጥፋቱ መጠን ለመጀመሪያ ጊዜ በጉባዔው ፊት ይገሰጻል በግል ማህደሩም ይመዘገባል። ለሁለተኛ ጊዜ ከ $50.00 (አምሳ ዶላር) መቀጫ ጋር ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። ለሶስተኛ ጊዜ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ግን ከዕድር አባልነቱ ይሰናበታል። የከፈለውም ገንዘብ ወይም ያበረከተው ስጦታ አይመለሰለትም።

11.4 በዕድሩ ላይ የማጭበርበር የእምነት ማጉደል ተግባር ፈጽሞ የተገኘ አባል ድርጊቱ በማስረጃ ከተረጋገጠበት የከፈለው ገንዘብ ሳይመለስለት ይሰናበታል። ከዕድሩ በማናቸውም ምክንያት ለሥራ የወሰደውን ንብረትም ሆነ ገንዘብ ይመልሳል እንዲሁም ይህንን ጉዳይ ለማስፈጸም ዕድሩ ያወጣው ወጪ (ገንዘብ) ካለ የመክፈል ግዴታ አለበት።

11.5 ከላይ በተዘረዘሩት ጥፋቶች ከአባልነቱ የተወገደ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይለት ለጠቅላላ ጉባዔው ይግባኝ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ይሆናል።

# አንቀጽ 12 - የዕድሩ የገቢ ምንጮች

12.1 ከአባሎች መመዝገቢያ

12.2 ከአባሎች ወርሀዊ ክፍያ

12.3 የዕድሩ አባሎች በሚፈጥሩት ልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች ማለትም ከግለሰቦችና ከድርጅቶች ወዘተ የሚገኘው ይሆናል።

# ክ ፍ ል አራት

# አንቀጽ 13 ድርጅታዊ አወቃቀር

ዕድሩ በሦስት እርከኖች የተዋቀረ የአመራር አካለት ሲኖሩት እነዚህም የጠቅላላ ጉባዔ፤ የአስተዳደር ቦርድ እንዲሁም የኦዲትና የቁጥጥር ኮሚቴ ይኖሩታል።

## 13.1 የጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ሐላፊነት

13.1.1 ጠቅላላ ጉባዔው፤ ዕድሩን በባለቤትነትና በበላይ አካልነት የሚመራና የሚቆጣጠር ወሳኝ አካል ይሆናል።

13.1.2 ጠቅላላ ጉባዔው በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል። ልዩ ስብሰባ በአስተዳደር ቦርዱ ወይም 1/3 ኛው አባላት ከጠየቁ ይጠራል። ስብሰባውን የሚመራው የቦርዱ ሊቀመንበር ይሆናል።

13.1.3 ጠቅላላ ጉባዔው የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴዎችን መርጦ የአስተዳድር ቦርድንና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላትን በዲሞክራሲያዊ ሂደት ምርጫውን ያከናውናል።

13.1.4 አስመራጭ ኮሚቴውም ሥራውን እንደፈጸመ ወዲያውኑ ለጉባዔው ውጤቱን ያሳውቃል።

13.1.5 ከግማሽ በላይ (51%) አባላት የተገኙበት ጠቅላላ ስብሰባ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

13.1.6 ጠቅላላ ጉባዔው ተጠርቶ ምልዓተ ጉባዔው ካልሞላ ሁለተኛ ስብሰባተጠርቶ የሚገኙት አባላት ከ 1/3 ኛ በላይ ከሆኑ ምልዓተ ጉባዔው እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡ እጅግ በጣም ወሳኝ ከሆኑ ማለት ከተራ ቁጥር

(13.1.12 እስከ 13.1.15) በቀር በተገኙት አባላት በመነጋገር ውሳኔ ማሳለፍ ይቻላሉ።

13.1.7 ሰባት አባላት ያሉት የአስተዳደር ቦርድና ሶስት አባላት ያሉት የቁጥጥር እና የኦዲት ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል በተጨማሪ 3 ተጠባባቂ የቦርድ አባላትንና አንድ ተጠባባቂ የቁጥጥር/ኦዲት ኮሜት አባል ጨምሮ ያዘጋጃል።

13.1.8 ከአባላት ለሚመረጡት ሰባት የአስተዳደር ቦርድ አስራ አራት እጩዎች እና እንዲሁም ከአባላት ለሚመረጡ ሦስት የቁጥጥር /ኦዲት ኮሚቴ ስድስት እጩዎች ለምርጫ ይቀርባሉ

13.1.9 ከቦርዱ አቅም በላይ የሆነ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም አስቸኳይ ጥሪ ይደረጋል ተሰብስቦ ይነጋግራል፣ይወስናል።

13.1.10 የቦርዱንም ሆነ የኦዲቲንግ ኮሚቴውን ሪፖርት አዳምጦ ተወያይቶ ይወስናል።

13.1.11 የዕድሩን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ መለወጥ ወይም ማሻሻል ባስፈለገ ጊዜ ቢያንስ የ 2/3 አባላት ቁጥር ያስፈልጋል።

13.1.12 የዕድሩን መተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ በ 2/3 የጉባዔው አባላት ሲጠየቅ ወይም ቦርዱ በቃለ ጉባዔ ተነጋግሮና ተስማምቶ ለጉባዔው ሲያቀርብ፣ ተሰብስቦ እንዲሻሻል የሕግ አርቃቂ ኮሚቴ መርጦ ከአስጠና በኋላ ሲቀርብለት በማረም ያጸድቃል።

13.1.13 የዕድሩን የሥራ ማስኬጃ በጀት ይፈቅዳል፣የአባላት አስተያይት ይስተናገዳል፣ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልሰና ማብራሪያ ይሰጣል።

13.1.14 ጥፋተኛ አባላትን ያሰናብታል፣የኦዲት ሪፖርትን አዳምጦ ይወስናል፣ ሪፖርቱን ያጸድቃል ወይም ይሽራል።

13.1.15 የዕድሩን ሕጋዊ ሰውነትና አገልግሎቱን ለማቋረጥ የጠቅላላ ጉባዔው 2/3 ኛ ድምጽ ያስፈልጋል።

## አንቀጽ 13.2- የአስተዳደር ቦርድ ሥልጣንና ሐላፊነት

13.2.1 የአስተዳደር ቦርድ የዕድሩን ዓላማ ለማስፈጸም በዚህ ደንብ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ተገቢውን ሁሉ ይፈጽማል።

13.2.2 ከቦርዱ ስላጣንና ሐላፊነት በላይ የሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙት ተሰብስቦ በመነጋገር ለጠቅላላ ጉባዔው ሪፖርት ያቀርባል።

13.2.3 ደንቡ በሚሰጠው ስልጣንና ሐላፊነት መሠረት ዕድሩን የሚመራ ሰባት አባላት ያሉት የአስተዳደር ቦርድ ይኖረዋል።

13.2.4 የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን ምርጫው የሚከናወነው በያዓመቱ በመጋቢት ወር ይሆናል።

13.2.5 አንድ የቦርድ አባል በተከታታይ ለሁለት የሥራ ዘመናት ብቻ በመመረጥ ሊያገለግል ይችላል፡፡

13.2.6 አንድ አባል የሥራ ዘመኑን ሳይጨርስ አገልግሎቱን በማንኛውም ምክንያት ቢያቋርጥ ለቀሪው የሥራ ዘመን እስከሚቀጥለው የምርጫ ጊዜ የሚያገለግል ማሚያ ከተጠባባቂ አባላት መካከል ቦርዱ በከፍተኛ ድምጽ የተመረጠውን እንዲያገለግል ያደረጋል። ለጠ/ጉባዔውም ያሳውቃል።

13.2.7 በማንኛውም የቦርድ አባላት ምርጫ ጊዜ የቦርዱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሆነ አባል ተመልሶ ለቦርድ አባልነት ቢመረጥ የወቅቱ ተመራጮች ከነባሮቹ ጋር በሚገናኙበት ጊዜ የሥራ ድልድሉ በአዲስ መልክ ይፈጸማል።

13.2.8 ለሁለት የሥራ ዘመን በተከታታይ ያገለገለ የቦርድ አባል በድጋሚ ለመመረጥ ቢያንስ ለአንድ የሥራ ዘመን (ሁለት ዓመት) መቆየት አለበት።

13.2.9 ከቦርድ አባላት መካከል ሦስት (3) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፡፡

13.2.10 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የዕድሩን የእለት ከእለት ሥራ እንዲሰራ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ከቦርዱ ውክልና ይሰጠዋል፡፡

13.2.11 የሥራ አስፈጻሚው ያከናወናቸውን የሥራ ዘገባ ለቦርድ ስብሰባ ያቀርባል፡፡

13.2.12 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚከተሉት ይሆናሉ

ሀ. ሊቀ መንበር፤

ሊ.ም/ሊቀ መንበር

ሐ.ዋና ጸሐፊ ናቸው

## 13.3 - ሊቀ መንበር

13.3.1 ሊቀ መንበሩ በማንኛውም ጊዜ የዕድሩ ተጠሪ ነው።

13.3.2 የጠቅላላ ጉባዔውንና የቦርዱንስብሰባዎች በሊቀ መንበርነት ይመራል።

13.3.3 ከዕድሩ ሂሣብ ሹም ጋር የዕድሩን ቼኮች ይፈርማል፣ ሂሣብ ሹሙ በሌለበት ጊዜ ከዋና ጸሐፊው ጋር በመሆን በቼኩ ላይ ይፈርማል።

13.3.4 በኮሚቴው የሥራ ክንውን ሪፖርትና በወጪና ገቢ ደብዳቤዎች ላይ ይፈርማል።

13.3.5 በዚህ መተዳደሪያ ደንብና በጠቅላላ ጉባዔው ወይም የአስተዳደር ቦርዱ በሚሰጡት መመሪያ መሠረት ዕድሩን በሚመለከት በማንኛውም ጉዳይ ዕድሩን ይወክላል። ከውጭ አካላት ጋር ዕድሩን ወክሎ ይነጋገራል።

13.3.6 የጠቅላላ ጉባዔውንና የአስተዳደር ቦርዱን ውሳኔዎች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

13.3.7 በአስተዳደር ቦርዱ አባላት አመራርነት ልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎች ሲመሰረቱ ሥራቸውን ይቆጣጠራል እገዛ ያደርጋል።

## አንቀጽ 13.4 - ም/ሊቀመንበር

13.4.1 ሊቀ መንበሩ በሌለበት ወይም መሥራት በማይችልበት ጊዜ የሊቀ መንበሩን ቦታ ተክቶ ከላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎች ሁሉ ያከናውናል ማለትም ሊቀ መንበሩ ያለው ስልጣን ሁሉ ምክትል ሊቀ መንበሩ ይኖረዋል ።

13.4.2 የሊቀ መንበሩ ረዳት በመሆን ዕድሩን ያገለግላል።

13.4.3 የዕድሩን አላማ ለማስፈጸም ያግዛሉ ተብለው በሚገመቱት ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ሁሉ ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር ወይም ሥራ አሥፈጻሚው ኮሚቴም ሆነ ቦርዱ በሚሰጡት ውክልና ይሰራል።

13.4.4 ንዑሳን ኮሚቴዎችን እንደአስፈላጊነቱ ይመሠርታል ለሥራቸውም መመሪያ ይሰጣል።

## አንቀጽ 13.5 ዋና ጸሐፊ

የአስተዳደር ቦርድ ጸሐፊ የሚከተሉት ሃላፊነት ይኖሩታል።

13.5.1 የጠቅላላ ጉባዔውንና የአስተዳደር ቦርዱን ቃለ -ጉባዔ ይይዛል።

13.5.2 ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር አጀንዳ ያዘጋጃል፤ መልዕክቶችንና የስብሰባ ጊዜዎችን ለአባላት በጽሁፍም ሆነ በሌላ መንገድ ያስታውቃል።

13.5.3 ወጪ መሆን የሚገባውን ገንዘብ በአስተዳደር ቦርዱ ስብሰባ ሲፀድቅ ለገንዘብ ያዡና ለሂሣብ ሹሙ በጽሁፍ ያሳውቃል።

13.5.4 ሰብሳቢውና ም /ሰብሳቢው በማይገኙበት ወቅት የአስተዳር ቦርዱን ስብሰባ ይመራል፡

13.5.5 የአባላትን መዝገብ ወቅታዊነት እየተከታተለ በመዝገብ ይይዛል።

13.5.6 ማንኛውንም የዕድሩን ሰነዶች ፣ማህተምና የፖስታ ሳጥን ቁልፍ ይይዛል።

13.5.7 ማንኛውንም በእጁ የሚገኙ የዕድሩ መዛግብት ቁጥጥር ኮሚቴው ለሥራ በሚፈልግበት ጊዜ በአግባቡ ማቅረብና ማስመርመር አለበት።

## አንቀጽ 13.6 - የሂሳብና የንብረት ሹም

13.6.1 የዕድሩን የሂሳብ መዛግብትና ደረሰኞች ይይዛል።

13.6.2 የተረጅዎችንም ሆነ ሌላ የክፍያ ቼኮችን ከሊቀመንበሩ ጋር ፈርሞ ያስረክባል

13.6.3 የዕድሩን ሂሳብ ሪፖርት ያዘጋጃል ያቀርባል።

13.6.4 የማህበሩን የሂሣብ መዛግብት፣ቼኮች፣ደረሰኞችን የኦዲት ኮሚቴው በሚፈልግበት ጊዜ ማቅረብና ማስመርመር አለበት።

13.6.5 የዕድሩን ሥራ ማስኬጃ በጀት ያዘጋጃል። ለቦርድ አቅርቦ ውይይት ተደርጎበት ወደ ጠ/ጉባዔው ቀርቦ ሲጸድቅም በሥራ ላይ እንዲውል ከገንዘብ ያዡ ጋር ይሰራል።

13.6.6 ወጪዎች በደንቡ መሠረት ወጪ መሆናቸውን ይከታተላል።

13.6.7 የዕድሩ ንብረት በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ይከታተላል።

## አንቀጽ 13.7 - ገንዘብ ያዥ

13.7.1 በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለዕድሩ ገቢ ሊሆን የሚገባውን ገንዘብ በየጊዜው እየሰበሰበ በዕድሩ የባንክ ሂሳብ ያስገባል።

13.7.2 ገንዘብ ያዡ የሥራ አገልግሎት ዘመኑን ሲጨርስም ሆነ በሌላ ምክንያት ከቦታው ሲነሳ በእጁ ያለውን ገንዘብና ንብረት በኦዲተሮች አማካኝነት ለተተኪው ያስረክባል።

## አንቀጽ 13.8 - የሕዝብ ግንኙነት ሀላፊ

13.8.1 በማንኛውም ዕድሩን በሚመለከት ሁኔታ የሚደረገውን የማስተዋወቅ ሥራ ከጽሕፈት ቤቱ ጋር በመተባበር ያከናውናል።

13.8.2 የአባላትን ችግርና ቅሬታ ይከታተላል ችግሩንም ለአስተዳደር ቦርድ በጽሁፍ ያሳውቃል።

13.8.3 የዕድሩን ዓላማ ለማስፈጸም ከሚያግዙ ተመሳሳይ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመመስረት ጥቅምና እርዳታ የሚገኝበትን ሁኔታ ያጠናል ለቦርዱም ሪፖርት በማቅረብ ዕድሩ በተሻለ ሁኔታ አገልግሎት የሚያገኝበትን መንገድ ያመቻቻል።

13.8.4 የዕድሩ አሰራር የሚቀላጠፍበት ሁኔታ አጠቃላይ ጥናቶችን እያደረገ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል።

13.8.5 ዕድሩ ከጋራ ዋስትና ወይም መድህን (Group Insurance) ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ አጥንቶ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል።

13.8.6 የዕድሩን ደረ ገጽ (WebSite) የማቋቋሙን የማስተዳደሩንና የማሳደጉን ጥረት በኃላፊነት ይመራል።

13.8.7 የዕድሩን የዶሜይን ስም ያስመዘግባል ምዝገባውም እንዳያልፍበት በያዓመቱ አስፈላጊውን እድሳት ያደርጋል።

13.8.8 አግባብ ካላቸውና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ጠንካራና ጤነኛ ቤተሰብ ለመፍጠር የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል።

## አንቀጽ 13.9 - የማኅበራዊ ጉዳይ ኮሚቴ

13.9.1 በአባላት ላይ የሐዘን ችግር በደረሰ ጊዜ ከሐዘነተኞች ጋር በቅርብ በመወያየት አስፈላጊውን መስተንግዶ ያደርጋል።

13.9.2 ስለቀብር ቦታ፣ትራንስፖርት፣ፖሊስና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች ከመሰል ተቋማትና አገልግሎት ሰጭዎች ጋር ግንኙት በማድረግ አስፈላጊውን ጥናትና ክንውን ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል።

13.9.3 በእዝኑ ቤት አስተናጋጆችን ይመድባል ቁጥጥር ያደርጋል። አንቀጽ

## 13.10 - ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ

ሦስት አባልት ያሉት የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ በጠቅላላው ጉባዔው ይመረጣል። የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ የሚከተሉት ሐላፊነቶች ይኖሩታል።

13.10.1 በዓመት ሁለት ጊዜ የዕድሩን አጠቃላይ የአስተዳደር፤ የሂሣብና የንብረት ሁኔታ በመቆጣጣር ለጠቅላላ ጉባዔው ዝርዝር ዘገባ ያቀርባል።

13.10.2 የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት የሚፈጠሩ ችግሮችን በወቅቱ መፍትሄ እንዲያገኙ ያማክራል።

13.10.3 የዕድሩን መተዳደሪያ ደንብ በትክክል መከበሩንና የታቀዱት በጀቶች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል።

13.10.4 በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተመዘገቡትን መመሪያዎች በየደረጃው እየተመለከተ ሕገ-ደንቡ በትክክል መተግበሩን ይቆጣጠራል።

13.10.5 ከጥፋትና ከስህተት በፊት በንብረት፣ በፋይናንስ አያያዝና አስተዳደር ላይ ሀሳብ ይሰጣል።

13.10.6 ኮሚቴው መደበኛ የስብሰባ ቀኖች ይኖረዋል። ቢያንስ በወር አንድ ቀን ይሰበሰባል። ይሁን እንጅ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥምና ተጨማሪ ስብሰባ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በመነጋገር ይሰበሰባል።

13.10.7 ኮሚቴው በፈለገው ጊዜ የዕድሩን ገንዘብ፣ንብረትና የአስተዳደር ቦርዱን አሰራር ይመረምራል።

13.10.8 የኦዲትና የቁጥጥር ኮሚቴ የሥራ ዘመን ለሦስት ዓመት ሲሆን ምርጫ የሚከናወነው በመጋቢት ወር በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ዕለት ይሆናል።

## አንቀጽ 13.11 — የሥራ ክፍፍል

13.11.1 ኮሚቴው ራሱ በመመራረጥ፤ አንዱን ሰብሳቢ፤ ሁለተኛውን ጸሐፊና ሶስትኛውን አባል በማድረግ ይመዳደባሉ።

## አንቀጽ 13.12 - የሰብሳቢው ሃላፊነት

13.12.1 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴውን ይወክላል።

13.12.2 የኦዲተና ቁጥጥር ኮሚቴውን ሪፖርት ሁሉም አብረው ያዘጋጁትን ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል።

13.12.3 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴን ስብሰባ ይመራል።

## አንቀጽ 13.13 - የጸሐፊው ሃላፊነት

13.13.1 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴን ስብሰባ ቃለ -ጉባዔ ይይዛል።

13.13.2 የአባላትን ስም ዝርዝርና ሰነድ ይይዛል።

13.13.3 ከጠቅላላ ጉባዔውና ከአስተዳደር ቦርዱ ጋር የሚጻጻፏቸውን ሰነዶች በኮሚቴው ሥር መቀመጥ ካለባቸው በጥንቃቄ ያስቀምጣል።

# ክ ፍ ል አምስት

## አንቀጽ 14 የቅሬታ አቀራረብ ሥነ -ሥርዓት

14.1. በማንኛውም ምክንያት ቅሬታ ያለው የዕድሩ አባል ወይም ቡድን ቅሬታውን እንደክብደቱ ለሊቀ መንበሩ ወይም ለአስተዳደር ቦርዱ ያቀርባል። ሊቀ መንበሩ ወይም የአስተዳር ቦርዱም ከ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

14.2. በአስተዳደር ቦርዱ ውሳኔ ያልተስማማ አባል ወይም ቡድን ጉዳዩ ለጠቅላላጉባዔ እንዲቀርብለት በጽሑፍ ይጠይቃል። ጠቅላላ ጉባዔውም እንደጉዳዩ ክብደትእንዲሁም በአመችነት በልዩ ስብሰባ ወይም በመደብኛ ስብሰባ የሚሰጠው ውሳኔ የፀና ይሆናል።

14.3 ከዚህ በላይ ከቁጥር

14.1 እስከ 14.2 በተመለከተው መሠረት ሳይፈጸም የወንጀል ተገባር ካልሆነ በስተቀር ለፍርድ ቤት አይቀርብም።

# አንቀጽ 15 - አጠቃላይ ጉዳዮች

15.1 የዕድሩ ገንዘብ ፤ንብረት፤ቁሳቁስ በሙሉ በአግባቡ ተመዝግቦ ይያዛል። ብክነትና ጉዳት እንዳያገኛቸው ተገቢው ጥንቃቄ ሁሉ ይደረጋል። ይህንን ተግባር የሚያስፈጽመው የአስተዳደር ቦርዱ በጋራና ወይም በተናጠል የሥራ ድርሻቸው ይሆናል።

15.2 ከሌሎች አካላት ማለትም መንግስታዊ፤ድርጅታዊና ግለሰባዊ ከሆኑ አካላት ጋር የሚደረግ ግንኙነት የዕድሩ የበላይ አካል የሆነው ጠቅላላ ጉባዔው ውክልና በሰጠው በአስተዳደር ቦርዱ ሊቀ መንበር ወይም እርሱ በወከላቸው ግለሰብ /ግለሰቦች ሊሆን ይችላል።

15.3 ከባንክ ጋር የሚኖር ግንኙነት፤ የዕድሩ ፀባይ ሁልጊዜ ከባንክ ጋር አብሮ መስራትን ይጠይቃል፤ ስለሆነም የፋይናንስን ጉዳይ በተመለከተ በሂሳብ ሹሙ ግንባር ቀደምትነት የሥራ አመራሩ ተግባራዊ መሆን አለበት። ገንዘብ ከባንክ ማውጣትን በተመለከተ ግን ደንቡ ከወከላቸው ከሁለቱ የሥራ አስፈጻሚ አባላት ጋር ካልሆነ በቀር ብቻውን ፈርሞ ማውጣት አይችልም።

15.4 ደንብን መሻሻል (መለወጥ) የሚቻለው ሕጉ ከደረስንበት የእድገት ደረጃና ከካሊፎርኒያ ግዛት ሕግ ጋር የማይጣጣም ከሆነ ፤ የተፈለገውን ነገር ካላካተተ ወይም ሌላ አሳማኝ ሁኔታ ሲፈጠር ብቻ ነው።

15.5 ደንቡ ያላካተታቸውና መደረግ ያለባቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ፤ ቦርዱ በቃለ -ጉባዔ ተነጋግሮ በድምፅ ብልጫ መወሰንና ችግሩን መፍታት ይችላል። በመቀጠል ግን ለጉባዔው አቅርቦ ሕግ አርቃቂው እንዲያየውና ተስተካክሎ ሕግ ሆኖ በጉባዔው እንዲጸድቅ ይደረጋል።

15.6 አንድ የማንኛውም ኮሚቴ አባል በተለያዩ ምክንያቶች ከኮሚቴ አባልነቱ ሊለቅ ይችላል። ይህም የሚሆነው በችሎታ ማነስ፤ በራሱ ጥያቄ፤ በሥነ -ሥርዓት ጉድለትና ምስጢር ባለመጠበቅ በመሳሰሉት ሲሆን አፈጻጸሙ ግን በሰላማዊና በመተማመን መሆን አለበት።

15.7 በቡድን መከፋፈልና ችግር መፍጠር፤ በዕድሩ ሕልውና ላይ አደጋ የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ሲከሰቱ የሥራ አመራር ኮሚቴው ፈጣን እርምጃ ይወስዳል። ግለ -ሰቦቹን ያነጋግራል ወይም ተደማጭ የሆኑ የዕድሩ አባላትን በመምረጥና በማወያየት ችግሩን ማለሳለስና ማስወገድ ይቻላል።

5.8 ይህ ደንብ የምንኖርበትን አገር ሕገ -መንግስት፣ ልዩ ልዩ ደንቦችን ሥርዓቶችን ያከበረና የተከተለ መሆን አለበት።

ስለሆነም ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉሞ በካሊፎርንያ ግዛት ተቀባይነት ማግኘትና አትራፊ ባልሆነ ድርጅትነት መመዝገብ አለበት።

15.9 የዚህ ደንብ የመግባቢያ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወደ እንግሊዝኛ ይተረጎማል በትርጉም መከከል ልዩነት ቢኖር በአማርኛ ቋንቋ የሰፈረው የፀና ይሆናል።

15.10 የዕድሩ የሂሳብ ዘመን እ.ኤ አቆጣጠር በየዘመኑ ከጥር 01 እስከ ታህሳስ 31 (January 01 to December 31) ይሆናል።

15.11 በያዓመቱ መጨረሻ የገንዘብና የንብረት ቆጠራ በኦዲት ኮሚቴ ይደረጋል።

15.12 ይህ ደንብ ዕድሩ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ እየተገመገመ ቢያንስ በ 1/3 ኛው የአባላት ጥያቄ እንዲሁም በሥራ እንቅስቃሴው ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ተጠንተው ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ይሻሻ ላል ወይም ይከልሳል።

## አንቀጽ 16 - ዕድሩ የተቋቋመበት ጊዜና ቦታ

የኢትዮጵያውያን አንድነት ዕድር በካሊፎርንያ ግዛት ሳንታ ክላራ ካውንቲ በሳን ሆዜ ከተማ መስከረም 04 2007 ዓ.ም (SEPTEMBER 14/2014) ተመሠረተ።

## አንቀጽ 17 - ደንቡ የሚጸድቅበት ጊዜ

ይህመተዳደሪያደንብጠቅላላ የዕድሩ አባላት በድጋሜ (Amended) ተወያይተውበትና ተስማምተውበት ካጸደቁበት ከ መጋቢት 10 ቀን 2010 ዓ.ም (March 17 /2018) ጀምሮ የጸና ይሆናል።

የኢትዮጵያዊያን አንድነት ዕድር መተዳደሪያ ደንብ Mailing Address 7052 Santa Teresa Blvd #105 San Jose, Ca 95139 ድር ቢያብር አንበሳ ያስር የአባቶቻችን መሪ ቃል ነው። በዚህ የተነሳ በዕድሩ፣ በማኅበሩ፣ በዕቁቡ ተሳስረው በጋራ " ማኅበራዊ ኑሮአቸውን ይመሩ ነበር። እኛም በሰሜን አሜሪካ፣ በካሊፎርኒያ ግዛት፣ በሳንሆዜ አካባቢ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮ-አሜሪካዊያን ለብዙ ጊዜ የምንመኘውን ይህን ዕድር አቋቁመናል።

ይህ መተዳደሪያ ደንብ ቅዳሜ መጋቢት ፳፫ ቀን ፳፻፲፭ ዓ/ም (April 01/2023) እንደገና ተሻሻለ።